# ግልፅ ደብዳቤ

## ለክቡር ዶ/ር ቴድሮስ ኣድሃኖም

## የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር

በቅድሚያ ክቡርነትዎ በጤና ሚንስትርነትዎ ጊዜ በሠሩት መልካም ስራ ምክንያት የብዙሃን ኢትዮጵያውያን እናቶችና ህፃናት ህይወት ማትረፍ በማስቻልዎ ለሌሎች ሃገራትም ኣርኣያ የሚሆን መከላከል ላይ ያተኮረ የጤና ስርዓት በመዘርጋትዎ ላመሰግንዎ እወዳለሁ። ወደ ውጭ ጉዳይ ሚንስትርነት ከተዛወሩም በሁዋላ በብዙ ኣገራዊ ጉዳዮች ከልብ በመቆርቆር ደፋ ቀና ሲሉ በማየቴ፤ እንዲሁም በኣነጋገርዎም ሆነ በተግባርዎ ከብዙ የኢህኣዴግ ባለስልጣናት በተለየ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የሚታይብዎ በመሆንዎና ከፖለቲካዊ ጥቅም ይልቅ የኣገርና የህዝብ ፍቅርን የሚያስቀድሙ ሆነው ስለታዩኝ ከዚህ በታችየማነሳቸውን ሁለት ጉዳዮች በቅን ልቦናዎ እንዲመለከቱልኝ እማፀንዎታለሁ።

1. የመጀመሪያው ከሳውዲ ኣረቢያ በግዳጅ እንዲመለሱ የተደረጉ ኢትዮጵያውያንን በተመለከተ ነው።

የሳውዲ ኣረቢያ መንግስትና ኣንዳንድ ሰብኣዊነት የጎደላቸው የሳዑዲ ዜጎች በወገኖቻችን ላይ ያደረሱት ኢሰብኣዊ ተግባር ምን ያህል እንዳሳዘነዎ በተለያዩ የሚዲያ ተቋዋማት በተላለፈው አንድ ንግግርዎ ላይ ታዝቤያለሁ። ከዚያም በሁዋላ በድርጊቱ የተጎዱ ወገኖቻችንን ወዳገራቸው ለማስመለስ ቀን ተሌት መድከምዎን ኣይተናል። ሆኖም ግን እኚህ ወገኖቻችን የደረሰባቸው በደል እንዲካስ ምንም ኣይነት ህጋዊ ጥረት መስሪያ ቤትዎ አለማድረጉ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ያሳዘነ ነው። ጉዳዩ በቅርቡ በተካሄደው የኣፍሪካ መሪዎች ጉባኤ አለመነሳቱ መስሪያቤትዎ ለኢትዮጵያውያን ያለውን ክብር ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ነው። ኣንድ ኣገር ሕጋዊም ሆነ ኢሕጋዊ በሆነ መንገድ የመጡበትን ስደተኞች የማስወጣት ሙሉ መብት ቢኖረውም ስደተኞቹን እንደሰብኣዊ ፍጡር ማስተናድ ይኖርበታል። ህጋዊም ሆነ ሕጋዊ ያልሆነ ስደተኛ ሰብአዊ ክብሩ ሊዋረድ ኣይገባውም፣ ያፈራውን ሃብትና ንብረት ሊነጠቅ ኣይገባውም። ሃላፊነት የሚሰማው መንግስት የዜጎቹን ውርደት በይሁንታ ሊቀበል ኣይገባውም፤ የዜጎቹንም መብት ለማስከበር ህጋዊም ዲፕሎማሲያዊም ጥረት ሊያደርግ ይገባዋል። ስለሆነም መስሪያ ቤትዎ በተባበሩት መንግሰታት ምክርቤትና በሌሎች ኣህጉራዊና አለምኣቀፍ ተቋዋማት በኩል የሳውዲ መንግስት ተገቢውን ካሳ ይከፍል ዘንድ እንዲሁም ላደረሰው በደል በይፋ ይቅርታ ይጠይቅ ዘንድ ተፅእኖ ማድረግ ይገባዋል። ከህጋዊ መንገድ በተጨማሪ መንግስትና ህዝብ በጋራ በተለያዩ መድረኮች ተፅእኖ ማድረግ ይገባቸዋል። ክቡርነትዎ ይህን ጉዳይ በቀና ልብዎ እንዲመለከቱ እጠይቅዎታለሁ።

2. ሁለተኛው በኢትዮጵያና በኤርትራ መንግስታት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ነው።

ሰሞኑን የቀድሞ የዩናየትድ ስቴትስ ከፍተኛ ዲፕሎማቶች ተከታታይ ፅሁፎች አውጥተዋል። ከነኚህም ኣምባሳደር ኸረማን ኮሀን፣ ኣምባሳደር ዴቪድ ሺን፣ ኣምባሳደር ፕሪንስተን ሊይማን የሚጠቀሱ ናቸው። የነኚህ ተከታታይ ፅሁፎች ይዘትና መልእክት ዩናየትድ ስቴትስ ኢትዮጵያን ፣ ኤርትራንና የኣፍሪካ ቀንድን በተመለከተ የፖሊሲ ለውጥ እንድታደርግ የሚገፉፉ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ያመላክታል። የአሜሪካውያኑ ዲፕሎማቶች መልእክቶች ጥቅል መልእክት የኤርትራን ህዝብ ከችግር ለማውጣት የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ መንግስታት የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ እንዲቀበሉና እዲፈፅሙ ማሳሰብ ነው።፡ ለድንበር ኮሚሽኑ መቋዋቋዋም መሰረት የሆነው ደግሞ ባለ አምስት ነጥቡ የአልጀርስ ስምምነት መሆኑን ክቡርነትዎ

ጠንቅቀው ያውቃሉ። የአልጀርስ ስምምነት ከመነሻው በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ተቀባይነት ያላገኘ ከመሆኑ በተጨማሪ ስምምነቱ ተፈርሞ ቀለሙ ሳይደርቅ ኣብዛኞቹ የስምምነቱ ነጥቦች በኤርትራ በኩል መጣሳቸው የሚታወቅ ነው። በዚህ መሠረት ክቡርነትዎ በዚህ ጉዳይ የሚከተሉትን ሁለት ጉዳዮች እንዲመለከቱ በትህትና እጠይቃለሁ።

1. የአልጀርስ ስምምነት የኢትዮጵያን ጥቅም የማያስጠብቅ በመሆኑ እንዲሁም በሁለቱም ወገኖች በመጣሱ ውድቅ ተደርጎ የሁለቱንም ወገኖች መሰረታዊ ጥቅም የማይጎዳና ዘላቂ ሰላምና እድገት ሊያመጣ የሚችል ሁሉን አቀፍ አዲስ ስምምነት እንዲፈጠር መጣር
2. የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት ጥያቄ ከኤርትራ ጋር የሚደረጉ ማናቸውም ድርድሮች ዋነኛ ጥያቄ እንዲሆን ማድረግ

ክቡር ዶ/ር ቴድሮስ ኣድሃኖም፤ የኤርትራንም ሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ በውስጣቸው የኖሩ በመሆንዎ ከእርስዎ በተሻለ የሚያውቃቸው ኣይኖርም። ለሁለቱም ህዝቦች መልካም እንዲገጥማቸው እንደሚመኙም ጥርጥር የለውም። የኢትዮጵያን ሉኣላዊ የባህር በር መብት ያላስጠበቀ ማንኛውም ስምምነት ደግሞ ዘለቂ ሰላምም ሆነ መልካም ጉርብትና ያመጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይሆናል።

ኢትዮጵያዊ ታናሽ ወንድምዎ

መርስኤ ኪዳን

ከሜኔሶታ ሀገረ አሜሪካ

mersea.kidan@gmail.com